*እኔ የዚህ ጸሁፍ ፀሃፊ፣ የፖለቲካ ስሜቱም ፍላጎቱም ኖሮኝም አያውቅም። ወደፊትም አይኖረኝም። ምክንያቱም የአፍሪካ ፖለቲከኛ ለመሆን የሚያስፈልጉት ዋናዎቹ ፀባዮች 1ኛ. ወሸታምነት፣ 2ኛ ከሃዲነት፣ 3ኛ ሌብነት፣ አንዳቸውም ከኔ ተፈጥሮ ጋር ሰለማይሄዱ ነው። ስለዚህ ይህን ጸሁፍ ሳቀርብ፣ አንዱን የፖለቲካ ቡድን ለመደገፍ ውይንም አንዱን ለማጥላላት ሳይሆን፣ ከኃይለሥላሴ መንግስት ጀምሮ በኢትዮጵያ የመንግስት አስተዳደርንና የሕዝቡን ስሜት በመጠኑ ስለማውቅ፣ በኢትዮጵያዊነቱ የሚሰማኝን ቁጭትና ሃዘኔታ ለመግለጽ ግድ ብሎኝ ነው።*

*አሉላ ታሪኩ።*

# መለስና አጋሰሶቹ

ይድረስ የአገርና የወገን ጥፋት ለሆንከው ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊና እንደ አጋሰስ በመኖ ለገዛሃቸው

1. የሕዋዋት ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት
2. የኢሕአዴግ ነጻ አውጪ ግንባር ተብዬ ፓርቲዎች ሴንትራል ኮሚቴ አባላት
3. የሐገሪቱ ጦር አዛገሮች
4. ሚኒስቴሮች
5. የክልል ፕሬዜዳንቶች
6. ካድሬዎች
7. በየደረጃው በአስተዳደሩ መዋቅር ውስጥ የተሰገሰጋችሁ አጋሰሶች

ሰላምና ጤና ከእናንተ ይራቅ!

እንደሰው ለብሳችሁ ቆማችሁ ስትሄዱ በመታየታችሁ ብቻ እንደሰው የምትቆጠሩ አጋሰሶች! አጋሰስ መኖው እስከቀረበለትና አቅሙ እስካለው የተጫነውን ተሸክሞ ወደ ተነዳበት ይሄዳል። እናንተም መለስ ያቀረሸውን ሁሉ ነገር ይበጃል ወይስ አይበጅም ብሎ የሚያገናዝብ ጭንቅላት ስለሌላችሁ፣ እሱ የሚላችሁን በጭብጨባ ተቀብላችሁ በሕዝብና በአገር ላይ ታስፈጽማላችሁ።

ብልሁ መሪያችሁ በአንድ ወቅት ለጋዜጠኛ ጥያቄ መልስ ሲሰጥ፣ "እኔ የምሾመው የኔን ዓላማ የሚያስፈጽም መሆኑን በማየት እንጂ ትምሕርትና ዕውቀት አያሻውም። ገበሬ መሆን ይችላል" ብሎ ነበር። ስለዚህ እናንተ ሥልጣን ላይ የተቀመጣችሁት በችሎታ ሳይሆን የሊቁን መሪ ትዕዛዝ፣ ጉዳቱንም ሆነ ጥቅሙን ሳታገናዝቡ የምታስፈጽሙ ስለሆናችሁ ብቻ ነው። ለምትይዙት ኃላፊነት ስትመረጡ ለመለስ እንደሮቦት የምታገለግሉ መሆናችሁ ታምኖበት ነው፣ ስለሆነም ሌላው ሁሉ ቀርቶ ሁላችሁንም አንድ አዳራሽ ውስጥ አስገብቶ፣ አሁን አየር ኃይልን አዝዤ እዚህ አዳራሹ ላይ ቦምብ አስጥላለሁ፣ ከዛ ቃጠሎው ሲያበቃ በየጠረጴዛችሁ ላይ አንድ-አንድ ኪሎ ወርቅ ታገኛላችሁ ቢላችሁ፣ ሊቁ ብሏልና መሞታችሁን እንኳን ሳታስቡ በጭብጨባ ቤቱን አናግታችሁ ወርቅ ሊታፈስ አሁኑኑ ትዕዛዝ ስጥ የምትሉ ናችሁ።

ለዚህ የተመቻችሁ አጋሰስ ባትሆኑማ፣

1. አገር ተቆርሶ ሊሱዳን ሲሰጥ፣

2. አፄ ዮሐንስና ሌሎች ጀግኖች ያስከበሩትን ባሕላችንና ማንነታችን ሲሸጥ፣ በአገራችን የሳውዲ አረቢያ ሕግ ሲሠራ፣ ማለትም ሴቶች በጥቁር ጨርቅ ተሸፍነው ሲሄዱ ማየት፣
3. ልማት በሚል ስም አንድ ሄክታር በ $1 በማስከፈል የአክራሪ አስልምና አራማጅ አገሮች በሕዝቡ ችግር በመግባት ማንነቱ ተስማምቶ ሲሸጥ፣

ይህ ምግባሩ በጣም የሚያሳዝነው የነአፄ ዮሐንስ አስከሬን አውጥቶ ለውሻ እንደመስጠት የሚቆጠር ነው። እናም፣ እናንተስ ያው አጋሰስ ናችሁ። የኢትዮጵያ ሕዝብና መለዮ ለባሹ ግን ከዳር እስከዳር ልትነሳና አገርህን ልታድን ይገባል! በዙሪያችን ያሉት አገሮች ኢትዮጵያን ለመግዛት ብዙ ጥረው፣ ብዙ ገለውም ሞተውም ሳይሆንላቸው ቀረ። እንደውም፣ አፄ ዮሐንስ ሕይወታቸው ያለፈው ከደርቡሾች ጋር በተደረገው ጦርነት ነበር። አፄ ዮሐንስ በሃገራቸው ድርድር አያውቁም። ጉድ እያደር ነው እንዲሉ፣ ይህ ባለጌ ለገንዘብ ሲል፣ ስንት ሕይወት ያለፈበትን እንድ ጥየት ሳይተኮስ እየመራ ሲያስገባቸው የሕዋዋት ታጋዮችም ሕዝቡም ዝም ማለቱ በጣም የሚያሳዝንም፣ የሚያሳፍርም ነው።

በዘር መከፋፈሉ አልሰራ ሲለው በኃይማኖት ግጭት አገሯን ሊያጠፉት ሲነሳ፣ ምን ሕሊና ቢኖራችሁ ነው ዝም ብላችሁ የምታዩት? የናንትም በዛ፣ አጋሰስም ጥቅም አለው። እናንተ ሹሞች ግን ከዚያም ዝቅ ያላችሁ ናችሁ።

ትግራይን ለመገንጠል ሽር ጉድ ሲልም ዝም ብላችሁ ታዩታላችሁ። የትግራይ ሕዝብ ትልቁን አገሩን ትቶ ይህ ደደብ ከሚያዝጋጅለት አጥር ውስጥ ገብቶ የሚታሰርለት አይደለም። ዛሬም በመላ አገሩ እየተዘዋወረና ከወገኑ ጋር እየኖረ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ችግሩ የአስተዳደር በደል እንደነበር ይህ ባለጌም ያወራ ነበር። ስለሆነም የገባው ቃል ኢትዮጵያ በሕዝብ በተመረጠ መንግሥት እንደምትተዳደር፣ ደርግ ቢወድቅ የተወረሰ ንብረትህ ተመልሶልህ በሕግ ተተዳደራለህ ነበር። እናም ሕዝቡም ሠራዊቱም ተባብሮ በድል ለመግባት በቁ። ከዚያማ የኢትዮጵያ ሕዝብ የተረፈው የአህዮቹ ዕጣ ፈንታ ሆነ። አህዮች ጅብ ሲጮህ ድምጹን ሰምተው፣ እንዳንተ የተስፋ ልፍለፋ ማለት ነው፣ ጅቡን ፍለጋ ያዙና ለካ የነበርው ሰማይ ላይ ነበር፣ ወርደው ለማየት ጠጋ ብለው የማለሉለትን ጅቡን ለመስማት ምህላ ገብተው ጌታን እንድያወርድላቸው ልመናውን ተያያዙት። የለመኑትን የማይነሳው አምላክ አወረደላቸውና ከመሬት ድምጹን ሲሰሙት ፍለጋ ጀምረው አገኙት። አምላክን አመስግነው ቆመው ሲያዩት እየጮህ ወደነሱ እሩጫውን ተያያዘው።፡እነርሱም ደስ ብሏቸው እየጨፈሩ ሲጠብቁት እንደደረሰ የአንዱን አህያ ሆድ ዘረገፈውና የቀሩት ሸሽተው አመለጡ።፡የኢትዮጵያም ሕዝብ ከደርግ የባሰ አይመጣም ብሎ የአቶ መለስንም ቃል ኪዳን በማመን ምህላ ገብቶ ሕወዋት የሚባል ጅብ አመጣ።

እና የአህዮቹ ዕጣ ፍንታ ከጣመው እና እናንተ አጋሰሶች አገርና ሕዝብ የባለጌ መፈንጫ አድርጋችሁ የተረፉት የፈሰሰ ደምና የወደቀ አጥንት መቆርጠም ብቻ ነው። ዋናውን የሚበሉት አሮጌው ጅብ ስብሐት ነጋና ጌታችሁ መለስ ዜናዊ ናቸው። ድሮም “ሆዳም አገርና ወገን የለውም” ይባላል።

ኢትዮጵያ የሚያኮራ ታሪክ ያላት አገር ናት።፡ግን ያለመታደል ሆኖ ከዕድሜዋ ያለፈው 20 ዓመት በምግባረ ብልሹዎች የሚያኮራ ሊሆን አልቻለም። በዚህ ታሪክ ውስጥ እናንተ ወላጆቻችሁም የሚያፍሩባችሁና የነሱነታችሁን እንዲክዱ አትጠራጠሩ። የወለዱችኋቸውም ልጆች በስማችሁ ለመጠራት ያፍራሉ። ታሪክ እየተከተለ ያሸማቅቃቸዋል። የሰው ልጅ በሕይወቱ ዕድል ገጥሞት ለሠራው ሁሉ ቀሪው ታሪክ ብቻ ነው። ያ የተዘረፈ ሃብትም እንዳመጣጡ ይሄዳል። የብዙ እንባ ስላለበትም ለተረካቢውም መጥፌያም ሊሆን ይችላል።

ሊቁ መሪ ያንተ አገዛዝ፣ በየቀኑ ከምታወግዘው መንግስቱ ኃ/ማሪያም አመራሩ እንደማይሻል ልትረዳ ይገባሃል። መንግስቱ አሠረ፣ ገደለ፣ አገር አጠፋ። አንተም አሠርክ፣ ገደልክ፣ አገር አጠፋህ። ነገር ግን፣ መንግሥቱ በሐገር ዳር ድንበር ድርድር አያውቅም።፡ ለማንም የውጭ በዝባዥ አሳልፎ አይሰጣቸውም። ምክንያቱም እሱ እንደናንተና እንድጓደኞችህ እይነግድም። እንደናንት ካፒታሊስት ስርዓት ብሎ ኮሚኒዝም ስርዓት አያካሂድም። ሶሻሊዝም ስርዓት መሠረተ የባለሃብት ንብረት ወረሰ፣ ለሕዝብ አደረገ። ትርፍ ቤቶች ወርሶ ለተከራዩ 50% ቅናሽ አድረገ፣ የከተማና የገጠር ትርፍ መሬት ወርሶ የገጠሩን ላራሹ ገበሬ አፀደቀለት። የከተማውንም ማንም ኢትዮጵያዊ ሊሠራ በሚችለው የቤት ፕላን መጠን የመሐንዲስ ብር 30 ብቻ አየከፈለ

በባሌበተነት ተረክቦ ሠርቶ መኖር ጀመረ፡፤ ለቤት ሠሪዎች ሞርጌጅ ያበድር የነበረው ወለድ 7% ነበር፡፡ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ይበዛል ብሎ ወደ 4% ዝቅ እንዲል አስደረገ። ይህ ነበር የደርግ መንግስት፣ አንተ ግን ኢትዮጵያን በሙሉ አንድ ፓርቲ ንብረት አድርገህ በዓለም የሌለ ሕግ ቤት የሚሠራም የሠራም ንብረቱ ጣሪያና ግድግዳ ብቻ ነው ብለህ መሬቱን መቸርቸር ጀመርክ፣ እና እናንተ ናችሁ ደርግን ለማውገዝ አፋችሁን የምትከፍቱት? እፈሩ!

ስሙ፣ እናንተ አጋሰሶች፣ ደርግ ወገንን በጎሳ ለመከፋፈል ለሰከን አልሞከረም። ዳር ድንበር አስከብሮ፣ የነበረችውን ኢትዮጵያን እንዳለች ለእናነተ ለአጋሰሶቹ አስረከበ። እንደናንተ የአጼ ዮሐንስን ዘውድ መለስን የክፉ ዘር ነን ብለው አላቀረሹም። አንዱን ከሌላው አብልጠው አላዩም። በነግራችን ላይ አፄ ዮሐንስ የኢትዮጵያ እንጂ የትግራይ ብቻ ንጉስ አልነበሩም። ለወሬ የእርሳቸው ነን በሉ እንጂ፣ ከውርደት ውጪ ምንም አላመጣችሁም። አጼ ዮሐንስ የሞቱለትን ዳር ድንበር፣ ኃይማኖታቸውን የሸጣችሁ የባለጌ ጥርቅም መሆናችሁን የትግራይ ሕዝብም ያውቀዋል። እናንተ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ለማጥፋት ተከፍሏችሁ የመጣችሁ ናችሁ። በጣም የሚያሳዝነው፣ የቀረው ኢትዮጵያ ሲቃጠል፣ ትግራይ ትድናለች ብላችሁ በዚህ ደንቆሮና ቀፎ በሆነ ጭንቅላታችሁ ማሰባችሁ ነው። ወላፈኑ ቢያንስ ይደርሳታል። ግን ለናንተ ምንም ማለት አይደለም፣ ይህው፣ ሕዝብ ሲያልቅና አገር ሲጠፋ ብራችሁ ወደተቀመጠበት ትሄዳላችሁ። ይብላኝ ለቀሪው።

አቶ መለስ በጣም የሚያሳዝነው እኒህ አንተ ያሳቅክባቸውና ያዋረድካችው ንጉሥ አፄ ዮሐንስ የተፈሩም የተከበሩም ነበሩ። ዛሬ አንተና ሌሎች ባለጌ የትግራይ ልጆች እሳቸውን ለማዋረድ የሼሪያ ሕግ በኢትዮጵያ ይሠራ ጀመር። እስቲ ሊቁ መሪ፣ የትግራይ ሕዝብ መታወቂያ የሆነውን መስቀል አድርገህ ሳውዲ መንገድ ላይ ውጣ? አንገትህን በሰይፍ ነው የሚያለያዩልህ! አፄ ዮሐንስ ሕይወታቸውን ሰውተው ያገዱትን የሸሪያ ሕግ እናንተ ስግብግቦቹ ለገንዘብ ሸጣችሁት። በጣም ያሳፍራልም፣ ያሳዝናልም። ወ/ሮ አዜብስ ሴት ልጅ ለኃይማኖቷ በጣም ጠንካራ ነች፣ አንቺ ግን የዚህ ባለጌ ስግብግብነት ስለተጋባብሽ አብረሽ ባህልሽን ሸጥሺው፣ ያሳዝናል!

እሺ፣ ጀግናው አቶ መለስ፣ በቅርብ የግብፁ መሪ ሙባረክ ላይ ስትጎርር ኢትዮጵያ በታሪኳ ለወራሪ ተበግራ አታውቅም፣ ስለሆነም ሞክረንና ታሪካችንን አንደግመዋለን አልክ። መቼም ላፍህ ለከት የለው። ግም! ያ እኮ ይሆን የነበረው ዛሬ በስህተት እንዳንተ ያለ ሽንታም የተቀመጠበትን ወንበር የያዙት ጀግና መሪዎች ስለነበሩ ነው። በራሳቸው የሚተማመኑ፣ ሕዝቡን እንድ አድርገው ይመሩ የነበሩ ሕዝብን እንደ ልጃቸው ያዩ የነበሩ ናቸው። አንተ እኮ የሕዝቡ አንድ መሆን ያጠፋኛል ብለህ መበበታተንን ገና እንደመጣህ ነው የተያያዝከው። መንደር እንጂ አገር የሚለው ስሜት ባንተ በሊቁ ሞቶ የለም እንዴ? አየህ፣ የፈሪ ጭንቅላት የሚያስበው የዕለቱን ነው። ስለሆነም አገርና ሕዝብ ስታጠፋ ይህ ሁሉ አልታየህም። ዛሬ እንደቀድሞዎቹ መሪዎች አንተ ሕዝቡን ውጣ ብለህ መሣሪያ ብትሰጠው ወዳንተ ነው አዙሮ የሚመጣው።

ከዚህ ጥፋትህ የሚያድንህ አንድ ሰው እንኳን ተው ይህ አይሆንም የሚል ጭንቅላቱ በትክክል የሚያስብ ሰው አላስቀመጥክም። ሁሉን ትተህ፣ ፕሬዝዳንት አድርገህ ያስቀመጥከውን መቶ አለቃ ግርማን ውሰደው። ኢትዮጵያ ሰው ያጣች ይመስል በባትሪ አስፈልገህ፣ እራሱን ተሸክሞ መሄድ የማይችል፣ እስካበላህው አንተን እያደነቀ የሚኖር የጋማ ከብት አስቀመጥክ። አታፍርም? በሐሳብም ሊረዳህ፣ ፈሪነትህንም ሊያላቅቅህ፣ ከሕዝብ ሊያቀራርብህ የሚችል ሰው ማስቀመጥ ትችል ነበር። ግን አንተ የምትፈልገው ድንቁርናህን እያደነቀ ጭራሽ ወደ ገደል የሚመራህን ነው። ስለሆነም ያለፈውን ሃያ ዓመት በታሪክ ዓይን ባዶ አድርገህዋል። አንተንና ጓደኞችህን ላየ “ፈሪ እናቱ መሃጸን ውሃ ሆኖ ይቅር” ያሰኛል።

አቶ መለስ አባክህ እውነቱን ንገረን፣ ጀግናው ሕዋዋት እናንተ ናችሁ ወይስ እውነተኛው ወደ ትግራይ ተመልሶ አዲስ አበባ የገባችሁት የእንግዴ ልጆች ናችሁ? በዕውነት ግራ ያሚያጋባ ነው። በየትኛውም ሚዛን ጀግና አገሩንና ወገኑን ሲያስከብር እንጂ ሲያዋርድና አገርና ወገን ለብር ሲሸጥ ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም! ነጮቹ ኢትዮጵያን ብዙም አይወዱም።፡ለምን ብትል፣ ያንተን እንኳ የቀረው ኢትዮጵያዊ፣ አያት ቅድመአያቶቹ በጀግኖች መሪዎቻቸው አማካይነት የቅኝ ግዛትን ሙከራ ስለከሸፈባቸውና በዚሁም ኢትዮጵያዊ ሰለሚጎርርባቸው ነው። የቀድሞ ነገሥታቶች የኢትዮጵያ አርማ ብለው ባንዲራችን ላይ ያደረጉት የአየር

መንገዳችን መለያ አርማው አንበሳ ነበር። ጀግናው መጣሃ! ምስሉ ወርዶ የሚበላህ መሰለህ መሰለኝ፣ የአንበሳ ምስል አልይ ብለህ ሁሉንም አጠፋሀው።፡ይህ የነጭ ጌቶችህ ትዕዛዝ ነው። የኢትዮጵያዊን ጥራት አጥፋልን ተብለህ፣ ባንዲራው ላይ ቆሻሻ ደፋህበት። አውሮፕላኑ ላይ እንዳንተ ቀላል ላባ አደረግህበት። ሥራህን ላየ ሰው አንተን መሪ አድርገው የሕዋዋት አባሎች መምረጣቸው የሚያሳየው እራሱ ድርጅቱ ምስጥ እነደበላው ግንድ ባዶ መሆኑን ነው። ሕዋዋቶች እባካችሁ በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም የምለምናችሁ የአፄ ዮሀንስንና የትግራይ ሕዝብ ተወላጆች ነን ብላችሁ አትናገሩ። ለምን? ስድብ ስለሚሆን! ኢትዮጵያዊነት የመነጨው ከሰሜን ከመሆኑም በላይ፣ ይህን እውን ለማድረግ ከታገሉት አንዱ አፄ ዮሐንስና የትግራይ ሕዝብ ከሌሎቹ ወገኖቹ ጋር ሆኖ ነው። እናንተን የመሰለ ፈሪ የሰሩትን ታሪክ አፈረሳችሁት። ስለዚህ ሰው ሲጠይቃችሁ የቀጠሯችሁ ነጮችና አረቦች ከባህር ያወጣችሁ መሆኑን ተናገሩ።

ፕሬዚደንት ኢሳያስ ፕሬዚደንት ለመባል ሲል፣ ወንድም እህቶቻችንን ከትልቁ አገራቸው አውጥቶ ስርቻ የከተታቸው ሰው እንኳን አገር እየቆረሰ ወገኑን አባሮ ለሌላ ተቃዋሚ አታደራጁብኝ ብሎ ጉቦ አልሰጠም። ከባዕድ አገሮች ፍርፋሪ ለማግኘት አገሩንና ባህሉን አልሸጠም። ሕዝቡን በጎሳ የመከፋፈል በሽታ የለበትም። ኤርትራ እስካሁን የምትተዳደረው አንድ ሕዝብ፣ አንድ ባንዲራ ነው፡፤ ኩሩም ነው። እንዳንተው ግን፣ ሕዝቡ የከፈልውን መስዋዕትነት ባዶ አድርጎ፣ ለሥልጣኑ ሲል እያሠረ፣ እየገደለ ተቀምጧል።

ስለዚህ እኛም ጋር ንፁህ ኢትዮጵያዊ ተወላጆች የኢትዮጵያዊነት ስሜት የሌላቸውን አገር ለማጥፋት የተዘጋጁትን ልክስክሶች አባራችሁ አገራችሁን ተረክባችሁ በአህያ ስብስብ ሳይሆን በኔ አምልኩ የሚል ደደብ ሳታስገቡ፣ የተማሩና ውጤት ያላቸው ሥራ በሚሠሩ ምሁሮች በመጠቀም በወሬ ሳይሆን በተግባር አገራችንን አሳድጉ። የአገር ዕድገት ኮንዶሚኒየምና ፎቅ በመሥራት አይደለም። የመለስ አስተዳደር ረሃብ ለሚፈጀው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሱፍ አልብሱት የሚል ነው። ምክንያቱም ለውጪ እይታ እንጂ ለወገን ተብሎ የሚሠራ አንድም ነገር የለም። የራሱን መሠረት-ድህነት ረስቶ ደሃን ከአዲስ አበባ እያጠፋ ነው። በጣም ያሳዝናል! እሱ የየትኛው የአቶ ዮሐንስ ደጃዝማች ወይንም የራስ ልጅ እንደው ቢነግረን ጥሩ ነበር። ግን የድሮ የትልቅ ሰው ዘር ድሃ አይጠሉም፣ ኃይማኖታችንም አይፈቅድለትም። መለስ ግን የድህነት ሰራዊት ሲጨፍርበት ያደገ ስለሆነ ደሃን ከእይታው በማጥፋት ድህነትን የተበቀለው ይመስለዋል። ተመልሶ የሚመጣብህ እየመሰለህ ሌባና ስግብግብ ሆንክ። ግን ያው አዕምሮህ ትክክል ስላልሆነ እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ 99% ይህን አንተ የጠላህውንና ያደግክበትን ድህነት ይጋራሃል። ዛሬ ማዘንና መሥራት የነበረብህ አንተ ያሳለፍከውን ሕይወት ሌላው ላይ እንዳይደገም ነበር።

በነገርህ ላይ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ስለአመራሩ ብዙ ልትል ትችል ይሆናል። ከናንተ ግን የባሰና የዘቀጠ ሮኖም አያውቅም። ከሕዋዋት መምጣት በፊት የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ሆኖ በመላ አገሩ እየተንቀሳቀሰ እየተሳሰበ ለዘመናት ኖሯል። እናንተ ከሊቁ መሪያችሁ ጋር መጥታችሁ አንድ አይደላችሁም ተለያዩ የሚል ትምህርት ቤት ከፈታችሁ።፡ ለመሆኑ በየትኛው መሪ ዘመን የትኛው ጐሳ ተጠቀመ? በጣም ያሳዝናል! የሌለ ታሪክ ጽፋችሁ ታነባላችሁ። የትግራይስ ሕዝብ ከየትኛው ጎሳ የበለጠ ተበደለስ? የትኛውስ ጎሳ ነው በዘሩ ከበረ፣ አደገ የምትለው?

በኢትይጵያዊነቴ ከልቤ አዝኜ ይህንን የከተብኩትን ጽሁፍ፣ በህዋዋት ውስጥ ያሉ ኩሩ ኢትዮጵያውያን አንብበው ከልባቸው እንዲጽፉት ምኞቴም፣ የዘውትር ጸሎቴም ነው!

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይጠብቅ!